ለዚሁ ሰውን ከፈጣሪው ለለየ ሃጢያት ጌታ እየሱስ ክርስቶስ እርስዎን ተክቶ ፍርድዎን ወስዶ እንደሞተልዎት እና እንደ ተነሳ ማመን ወደ ዘላለም ሕይወት ቀጥታ የሚያስገባዎት መንገድ ነው ይህም እግዚአብሔር የዘላለም ፍርድ ከእርሶ ላይ ወስዶ በልጁ በእየሱስ ክርስቶስ ላይ በማድረግ አለም ሁሉ በልጁ አማካይነት እንዲድኑ እንጂ እንዳይጠፉ ያደረገውን ስጦታ በቀጥታ እንዲቀበሉ ያደርጎታል ማለት ነው፡፡ በመጨረሻም እየሱስን የግል አዳኝና ጌታ አድርገው በመቀበል የልብዎን ስፍራ ቢሰጡት በዘላለም መንግስት ውስጥ ቅዱሳን ባሉበት ለመሆን ከመሞትዎ በፊት ያረጋገጡት ትክክለኛና የመጨረሻ ውሳኔዎ ይሆንሎታል፡፡

‹‹ሮሜ 10፡13... የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል”...ይላል”በዚህ ምድር ያልዎት እድሜ 1000 አመት እንኳን ቢሆን አጭር መሆኑን አይዘንጉ ህይወትዎን ለማዳን እግዚአብሔር ያቀረበልዎትን ጥሪ ተቀብለው ከፍርድ ለመዳን ውሳኔ ማድረግ የእርስዎ ሃላፊነት ነው፡፡ ‹‹ዕብ 9፡27... ለሰዎች አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደተመደበባቸው እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ የብዙዎችን ሃጢያት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሰዋ በኋላ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ሃጢያት ይታይላቸዋል”... ይላል

ይህን ጽሁፍ አንብበው በእርስዎ ፈንታ የሞተልዎትን ጌታ በመቀበል ከፍርድና ከኩነኔ በማምለጥ የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ከወሰኑ በዚህ ጽሁፍ ባለው አድራሻ ስምዎንና አድራሻዎን ቢልኩልን መንፈሳዊ ጽሁፎችን በነፃ ልንልክልዎት እንችላለን ከvancouver ውጪ ከሆኑ ደግሞ በአቅራቢያዎ ካለ ቤተ ክርስቲያን ጋር እንዲገናኙ ልንረዳዎት እንችላለን፡፡

‹‹ጌታ ሆይ! ‘በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም” ባልከው መሠረት የኃጢያት ይቅርታ ለመቀበል በቀጥታ ወደ አንተ እቀርባለሁ፡፡ ኃጠያተኛ እንደሆንኩ አውቃለሁ፡፡ ስለ ኃጢያቴ ስትል በመስቀል ላይ ደምህን እንዳፈሰስክልኝ አምናለሁ፡፡ ከልጅነቴ ጀምሮ እስከዚች ደቂቃ ድረስ የሠራሁትን ኃጥያት በሙሉ ይቅር በለኝ፡፡ በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሸክም ሁሉ እንሳልኝ፡፡ ጌታ ሆይ ና! ወደ ልቤ ግባ፣ የሕይወቴም አዳኝና ጌታ ሁን፣ አሜን፡፡”

ይህንን ጸሎት ከልብ ከጸለዩ ጌታ ኢየሱስ በቃሉ እንደተናገረው ወደ ሕይወትዎ በመግባት የእግዚአብሔር ልጅ አድርጎ ተቀብሎዎታል፡፡

“ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፡፡” (ዮሐንስ 1:12).

www.operationezra.com

በምድር የቀረዎት እድሜ ጥቂት ደቂቃ ቢሆንስ?

ይህችን አጭር ጽሁፍ አንብበው እስኪጨርሱ በአለም ላይ 900 ሰዎች በሞት እንደሚሰናበቱ ያውቁ ይሆን?

በአለም በአንድ ሰኮንድ ጊዜ ውስጥ ሶስት ሰዎች ከዚህ አለም በሞት ይለያሉ ተብሎ ይገመታል። ያም ማለት ይህችን አጭር የፈጣሪዎን የህይወት ጥሪ የምታበስርልዎትን ጽሁፍ አንብበው በጨረሱ ጊዜ በግምት ወደ ዘጠኝ መቶ ሰዎች ከዚህ ዓለም በሞት ይለያሉ ማለት ነው። የማንም ሰው ዕጣ ፈንታ ጾታ ሳይለይ በዚች ጊዜ ውስጥ ተወስኗል። ትንሽም ሆነ ትልቅ፣ ሀብታምም ሆነ ድሀ፣ የተማረ ሆነ ያልተማረ በዚች ጊዜ በማንም ላይ ድንገት ሊመጣ ከሚችለው ሞት ከሚባል የሰው የምድር ታሪክ ማብቂያ ማምለጥ እንደማይቻል እንረዳለን።

በዚች ምድር የመኖርዎ የመጨረሻ ሰዓት አሁን ቢሆንስ? ... አዎ! ማን ያውቃል? በዚህ ምድር ቀጥሎ ባለችው ሰኮንድ ለመኖር እርስዎ ሊወስኑ አይችሉም። በሚኖሩበት አካባቢ በዚህ ሰዓት አንድ ሰው ሊሞት እንደሚችል የሚያውቁ ከሆነ እርስዎንም ጨምረው ማሰብ ይኖርቦታል።

ዕድሉ የእርስዎ ሆኖ ሁሉን ነገር ትተው ድንገት በሞት ቢለዩ ሕይወት በሌለበት ሥጋዎ የቀብር ስነሥርዓት እንዲሁም በምድር በነበሩበት ጊዜ በጽሑፍ ከሚነበብ የሕይወት ታሪክዎ በስተቀር ዘመድና ወዳጆችዎ ከእርስዎ ለተለየችው ዘላለማዊ ነፍስዎ የሚያደርጉላት ነገር የለም።

በዚህች ቅጽበታዊ ጊዜ ውስጥ ሁሉ ነገር በእንዲህ ዓይነት መልክ የሚጠናቀቅ ከሆነና ጊዜያዊውን ዓለም ትተው ዘላለማዊውን ለመገናኘት ለሞት ተረኛው እርስዎ ከሆኑ ከዚህ በኋላስ የት ይሄዳሉ? ሲኦል ወይስ መንግስተ ሰማይ? የሚለው አንገብጋቢ ጥያቄ እርግጠኛ መልስ ማግኘት ይኖርበታል። ስጋዎ የት እንደሚሄድ አስቀድመው ካወቁ መንፈስዎና ነፍስዎ የት እንደሚሄዱ ሳይሞቱ ሊያውቁና አሁኑኑ ሊወስኑ እንደሚገባዎ መልስ ሊሰጥዎት የሚችለው የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው።

አንዴ ከሞቱ በኋላ በሥጋዎ ላይ አቅም እንዳልነበረዎት እንዲሁ አንዴ ከሞቱ በኋላ ከፈጣሪዎ ጋር ለመታረቅ ዕድሉ አይኖርዎትም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ሰው በሥጋው እያለ ስለዘላለማዊ ሕይወቱ እንዲወስን አስቀድሞ የምሥራች ወንጌል እንዲሰማ እና አምኖ እንዲድንበት ጥሪ አቅርቦሎታልና። ምርጫው በእርስዎ እጅ ነው። እግዚአብሔር ለሰው የመምረጥ ፈቃድ ሰለሰጠው አያስገድድዎትም።

‹‹በዮሐንስ ራዕይ 22 ቁ ፲፩ ... አመጻኛው ወደፊት ያምጽ፣ ርኩሱም ወደፊት ይርከስ፣ ጻድቁም ወደፊት ጽድቅ ያድርግ፣ ቅድሱም ወደፊት ይቀደስ አለ ... ይላል። በዘዳግም ፲፩ ቁ 26 ደግሞ ...እነሆ ዛሬ በፊታችሁ በረከትና መርገምን አኖራለሁ፣ በረከትም እኔ ዛሬ ለእናንተ የማዘውን የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ብትሰሙ መርገምም የአምላካችሁን ትዕዛዝ ባትሰሙ ... ይላል"።

ታድያ ፈቃድዎን ለሞት ወይም ለህይወት ለመስጠት መብቱን ፈጣሪ ለራስዎ በዚህ መልክ ከደነገገልዎ አሁን ይህ ጊዜ ሳያልፍቦትና ሞት ሳይመጣ ዛሬ በስጋ አካል እያሉ ምርጫዎ ምን ይሆን?

ምርጫዎ ሲኦል ከሆነ ምንም የሚያደርጉት ነገር የለም። እስካሁን ከእናታችን ማህፀን ጀምሮ ሃጢያተኞች እንደሆንን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ‹‹በሮሜ 6፥23 ላይ…የሃጢያት ደመወዝ ሞት ነው…ይላል፤ መዝሙር 9፥17… ሃጢያተኞች ወደ ሲኦል ይመለሳሉ"… ይላል ምርጫዎ የዘላለም ሕይወት ከሆነ ግን የሚከተሉዋቸው ነገሮች አሉ እነርሱም ፦

በመጀመሪያ ሃጢያተኛ መሆንዎን ማመን አለብዎት ‹‹ሮሜ 3፥23... ልዩነት የለምና ሁሉም ሃጢያትን ሰርተዋልና የእግዚአብሄርም ክብር ጎድሎዋቸዋልና"... ይላል

ሁለተኛ ከሃጢያተኛነትዎም የተነሳ ሞት ለሁሉ ሰው የደረሰ እንደሆነ ማመን አለብዎት

‹‹ሮሜ 5፥12... በዚህ ምክንያት ሃጢያት በአንድ ሰው ወደ አለም ገባ በሃጢያትም ሞት እንደዚሁም ሁሉ ሃጢያትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ"... ይላል።

ሶስተኛ ስለ ሃጢያትዎ ንሰሃ መግባት ነው።

‹‹ሕዝ 33፥፲፩... ሃጢያተኛው ከመንገዱ ተመልሶ በህይወት ይኖር ዘንድ እንጂ ሃጢያተኛው ይሞት ዘንድ አልፈቅድም"... ይላል

የመዳን ቀን ዛሬ ነው!